20ኛ ዓመት ቁጥር 14
20th Year No. 14

ባሕር ዳር ሰኔ 06 ቀን 2007 ዓ.ም
Bahir Dar 13 June, 2015

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ
የአማራ ብሔራዊ ክልል ምክር ቤት

# ዝክረ ሕግ
# ZIKRE HIG

## Of the Council of the Amhara National Regional State in the Federal Democratic Republic of Ethiopia

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

Issued under the auspices of the Council of the Amhara National Regional State

✉ 1324
ያንዱ ዋጋ 8.90 ብር
Unit Price Birr 8.90


**ማውጫ**

**አዋጅ ቁጥር 226/2007 ዓ/ም**

**የተሻሻለው የአማራ ብሔራዊ ክልል ከተሞች ማቋቋሚያ፣ ማደራጃና ሥልጣንና ተግባራት መወሰኛ አዋጅ እንደገና ማሻሻያ አዋጅ**

**Content**

**Proclamation No.226/2015**

**The Revised Proclamation for the Establishment, Organization and Determination of Powers and Duties of Urban Centers Re-ammendment Proclamation of the Amhara National Region**


## አዋጅ ቁጥር 226/2007 ዓ/ም

### የተሻሻለዉ የአማራ ብሔራዊ ክልል ከተሞች ማቋቋሚያ፣ ማደራጃና ሥልጣንና ተግባራትን ለመወሰን የወጣ አዋጅ

በስራ ላይ ያለውን አዋጅ ቁጥር 91/1996 ዓ.ም/ እንደተሻሻለ/ መነሻ በማድረግ በብሔራዊ ክልሉ ዋና ዋና ከተሞች ማለትም በባህር ዳር፣ በጎንደርና በደሴ ምክር ቤቶች አማካኝነት ተቋቁመው የዳኝነት አገልግሎት በመሥጠት ላይ የሚገኙት የከተማ-ነክ ጉዳይ ተመልካች ፍርድቤቶች ተጨማሪ የሥረ-ነገር ሥልጣን ተሠጥቷቸው የመደበኛ ፍርድ ቤቶችን መጨናነቅ በሚቀንስ አኳኋን የተገልጋዩን ህብረተሰብ ችግር እንዲያቃልሉ ማድረግ ተገቢ ሆኖ በመገኘቱ፤

## Proclamation No.226/2015

### A Revised Proclamation Issued to Provide for the Establisment, Organization and Determine Powers and Duties of Urban Centers of the Amhara National Region

WHERE AS, It has been found necessary to mittigate the problems of the clients of courts, that are pertinent to render judiciary activites of urban cases, established pursuant to the National Region main cities of the Councils of Bahir Dar , Gondar and Dessie , starting from the revised proclamation No 91 /2003 which is in effect, rendered additional jurisdiction power in a way of decreasing crowdedness of the regular courts;

ይህንኑ ለማከናወን እንዲቻል ቀደም ሲል በየከተማ ምክር ቤቶቹ በኩል ተሻሽሎ የወጣውና የእነዚሁ ፍ/ቤቶች ስልጣን የተዘረዘረበት ደንብ ያካተታቸው አንዳንድ ተጨማሪ ፍታብሔርነክና የወንጀል ጉዳይ ድንጋጌዎች ከእናት የከተሞቹ ማቋቋሚያ አዋጅ ጋር የማይጣጣሙ ሆነው ከመገኘታቸው የተነሣ ይህንኑ ተቃርኖ የሚያስወግድ ማስተካከያ ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

Where as, it has been found necessary to remove the contradiction of the regulation that has been listed down power of these courts, that included some additionl civil and criminal cases provisions, with that of the main cities establishment proclamation, that has been issued in revision by each urban councils previously possible to conduct it;

ለዚሁ ያመች ዘንድ ለጉዳዩ በቀጥታ አግባብነት ያላቸውን የአዋጁን ድንጋጌዎች በማሻሻል የከተማ-ነክ ጉዳይ ፍርድቤቶች በከተማው ክልል ውስጥ የሚመነጩትን ማዘጋጃቤት-ነክ ጉዳዮች መርምረው እንዲዳኙ ከሚጠበቅባቸው ቁልፍ ሀላፊነት ጋር በተጣጣመ ሁኔታ እንደ ሌሎች አቻ የሀገሪቱ ከተማ ነክ ፍ/ቤቶች ሁሉ ስነስራታዊ ጠባይ ያላቸውን አንዳንድ የፍታሐብሔር፣ የወንጀልና የደንብ መተላለፍ ክሶችንና አቤቱታዎችን ደርበው እንዲመለከቱ ቢደረግ እርምጃው የመደበኛ ፍ/ቤቶችን ጫና ከማቃለሉም በላይ ለየከተማው ኗሪ ህብረተሰብ የፍትህ ተደራሽነትን እንደሚያሰፋና እንደሚያሣልጥ የታመነበት በመሆኑ፤

WHERE AS, it has been believed that taking measures shall widen and speed up justice accessibility for urban society more than mittigating the burdens of the regular courts, if urban case courts shall see some civil, criminal and violation of regulation charges and complaints, in addition that have procedural conduct like other urban case courts of the country, in line with a key responsibility of investigating and giving decision of initiating municipality cases in urban places, by revising provisions of the proclamation that are in line with it.

የአማራ ክልል ምክር ቤት በተሻሻለው የብሔራዊ ክልሉ ህገ-መንግሥት አንቀጽ /49/ ንዑስ አንቀጽ 3/1/ድንጋጌ ሥር በተሠጠው ሥልጣን መሠረት ይህንን አዋጅ አውጥቷል።

NOW, THEREFORE, the council of the Amhara Region, vested with power in it by Article 49, sub-article 3/1/ of the revised constitution of the National Region, shall issue this praclamation.

1. **አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "የተሻሻለው የከተሞች ማቋቋሚያ፣ ማደራጃና ሥልጣንና ተግባራት መወሰኛ አዋጅ እንደገና ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 226/2007ዓ/ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. **ማሻሻያ**

የተሻሻለው የአማራ ብሔራዊ ክልል ከተሞች ማቋቋሚያ፣ ማደራጃና ሥልጣንና ተግባራት መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 91/1996 ዓ/ም /እንደተሻሻለ/ በዚህ አዋጅ እንደሚከተለው በድጋሚ ተሻሽሏል፦

**ሀ. የአዋጁ አንቀጽ /57/ ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀፅ /57/ ተተክቷል፡-**

**57) ስለ ፍርድ ቤቱ የፍትሐብሔርና የወንጀል ዳኝነት ስልጣን**

1. የከተማ ነክ ጉዳዮች ፍርድ ቤት ከዚህ በታች በተመለከቱት ፍትሐብሔር ነክ ጉዳዮች ላይ የተሟላ ከባቢያዊና የስረ-ነገር ዳኝነት ስልጣን ይኖረዋል፡-

ሀ/ የከተማውን መዋቅራዊ ፕላን አጠባበቅ፣ የመሬት ይዞታ ባለመብትነት፣ የህንፃ ግንባታ ፈቃድ አሰጣጥ፣ የቦታ አስተዳደርና አጠቃቀም ሕግጋት፣ ደንቦችና መመሪያዎች አፈፃፀምን የሚመለከቱ ጉዳዮች ፤

ለ/ ከከተማው አስተዳደር አስፈፃሚና የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት ሰጭ አካላት የመቆጣጠር ስልጣንና ተግባር ጋር በተያያዘ የሚነሱ ክሶች፤

1. **Short Title**

This proclamation may be cited as "the Revised Proclamation for the Establishment, Organization and Determination of Powers and Duties of Urban Centers Re-ammendment Proclamation No. 226/2015."

2. **Ammendment**

The Revised Proclamation for the Establishment, Organization and Determination of Powers and Duties of Urban Centers of the Amhara Nationsl Regional Proclamation No.91/2003 /as ammended /is re-ammended as follows by this proclamation:

**A. Article /57/ of the proclamation is deleted and replaced by the following new Article /57/:**

57) **Civil and Criminal Jurisdiction of the Court**

1. The city court shall have exclusive surrounding and jurisdiction power on civil cases stipulated herein under:

a/ preservation of the city structural paln, land witholding right, building construction licencing , land administration and use laws, cases which concerning implementation of regulations and directives;

b/ Rasing charges related with powers and duties of supervision of the city administration executive and municipality service delivery bodies;

ሐ/ የማዘጋጃ ቤት ግብር፣ቀረጥና የአገልግሎት ክፍያዎችን አወሳሰንና አሰባሰብ የተመለከቱ ጉዳዮች፤

መ/ የከተማው አስተዳደር አስፈፃሚ እና የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት አካላት ወይም በከተማው አስተዳደር ባለቤትነት ስር ያሉ ተቋማት የሚገቡዋቸውን አስተዳደራዊ ውሎች አፈፃፀም በተመለከተ የሚነሡ ጉዳዮች፤

ሠ/ በከተማው አስተዳደር አስፈፃሚ እና የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት አካላት ወይም በከተማው አስተዳደር ሌሎች ተቋማት መካከል የሚነሱ ክሶች፤

ረ/ በከተማው አስተዳደር ባለቤትነት ስር የሚተዳደሩ ሆነው ለንግድ፣ ለመኖሪያ ወይም ለሌላ አገልግሎት በማዋል ላይ ካሉ የመንግስት ቤቶች ጋር በተያያዘ የሚነሱ ክሶች፤

ሰ/ በንግድ ውድድርና የሸማቾች ጥበቃ አዋጅ ቁጥር 813/2006 ዓ.ም አንቀፅ /34/ መሠረት የከተማው የሸማቾች ጥበቃ የዳኝነት አካልና የዚሁ ይግባኝ ሠሚ አስተዳደራዊ ፍ/ቤት እስከሚቋቋሙ ድረስ በአዋጁ አንቀጽ /32/ ስር የሚወድቁ ፍትሐብሔር ነክ ጉዳዮች፤

ሸ/ በከተማ መሬት ይዞታ ምዝገባ አዋጅ ቁጥር 818/2006 ዓ.ም መሠረት የተቋቋመው የመሬት ይዞታ ማረጋገጥ ቅሬታ ሰሚ ጉባኤ በዚሁ አዋጅ አንቀጽ /17/ ንዑስ አንቀጽ /3/ እና /4/ ድንጋጌዎች መሠረት የሚሰጣቸውን ውሣኔዎች በመቃወም የሚቀርቡ አቤቱታዎች፤

c/ cases pertaining to muncipality taxes, dues and determination and collection of service charges ;

d/ Raising cases pertaining to the implementation of administrative contracts, that the city administration executive and municipality service delivery bodies, or institutions under the city administration ownership;

e/ Raising charges by the city administration executive and municipal service delivery bodies, or among other institutions of the city administration;

f/ Raising charges related with government houses, that serve for trade, residence or other services, that administred under the ownership of the city administration;

g/ pursuant to Article /34/ of the Trade Competition and Purchasers' Protection Proclamation No 813/2014, civil cases under Article /32/ of the proclamation, until the establishment of the city purchasers protection judicial body and administration appealate court;

h/ The would be submitted complaints in conravene with rendering decisons, pursuant to sub –article /3/ and /4/ of Article /17/ of this proclamation, that of the established grievance committe assurance of land withholding registration proclamation No. 818/2014;

ቀ/ የስም ለውጥ አቤቱታ፤

በ/ የወራሽነት፣ የባልነት ወይም የሚስትነት፣ የአሳዳሪነት ወይም የሞግዚትነት ምስክር ወረቀት ለማግኘት የሚቀርብ አቤቱታ፤

ተ/ የመጥፋት ውሣኔን ለማሰጠት የሚቀርብ ክስ ፡፡

2. ፍ/ቤቱ በወንጀልና በደምብ መተላለፍ ረገድ ከዚህ በታች የተመለከቱትን ጉዳዮች ተቀብሎ የመመርመርና የመዳኘት ስልጣን ይኖረዋል፡-

ሀ/ የከተማው አስተዳደር በህግ በተሰጠው ስልጣን መሠረት እየወሰነ ከሚሰበስባቸው የማዘጋጃ ቤት ግብር፣ ቀረጥና የአገልግሎት ክፍያዎች አፈፃፀም ጋር በተያያዘ የሚነሱ የወንጀል ክሶች፤

ለ/ የትራፊክ ደምብ መተላለፍን የሚመለከቱ ክሶች፤

ሐ/ ጤናና የአካባቢ ንፅህና አጠባበቅን የሚመለከቱ ጉዳዮች፤

መ/ በከተማው አስተዳደር ልዩ ልዩ አስፈፃሚ አካላት አማካኝነት የሚሰጡ የደንብ መተላለፍ ቅጣት ውሣኔዎችን ለማስፈፀም የሚቀርቡ ክሶች፤

i/ Renaming complaints;

j/ complaints that shall be submitted to get the certificate of the heirs, spouses, guardian or tutor;

k/ Charges that shall be submitted, cause to render declaration of absence.

2. The court shall have a power of investigation and jurisdiction by receiving cases that are stipulated herein under, on the way of crime and violation of regulation:

a/ Criminal charges that shall be raised related with the implementation of municipal taxes, dues and service charges, that the city administration collects deciding, pursuant to the rendered vested power with law;

b/ charges of the traffic petty offence;

c/ Cases related with health and environmental sanitation;

d/ Raising charges, cause to execute the rendered offensive decisions of violation of traffic regulation, pursuant to the city administration various executive bodies;

ሠ/ በቀበሌ ማህበራዊ ሸንጎዎች አማካኝነት እንዲታዩ ተሻሽሎ በወጣው የእነዚሁ ሸንጎዎች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 151/2000 ዓ/ም አንቀጽ /13/ ሥር የተወሰኑትን ሣይጨምር በኢፌዴሪ የወንጀል ሕግ 7ኛና 8ኛ መጻሕፍት ውስጥ የተመለከቱ ሌሎች የደንብ መተላለፍ ጥፋቶች /ከ734-865/።

**ለ. ከአዋጁ አንቀጽ /57/ ቀጥሎ የሚከተሉት አዳዲስ አንቀጾች /58/ ፣ /59/ እና /60/ የገቡ ሲሆን በነዚሁ አዳዲስ ድንጋጌዎች መግባት ምክንያት ከአንቀጽ /58/ እስከ /71/ ያሉት ድንጋጌዎች ከአንቀጽ /59/ እስከ አንቀጽ /73/ በመሆን ወደፊት ተሸጋሽገዋል፡-**

## 58) ፍ/ቤቱ በይግባኝ ሰሚነት አቋም ስለሚኖረው ተጨማሪ ስልጣን

የከተማ ነክ ጉዳዮች ፍ/ቤት በይግባኝ ሰሚነት አቋሙ ከዚህ በታች የተመለከቱትን ተጨማሪ ጉዳዮች በይግባኝ የመዳኘት ስልጣን ይኖረዋል፡-

1. የከተማ ቦታን በሊዝ ስለመያዝ በወጣው አዋጅ ቁጥር 721/2004 ዓ.ም አንቀጽ /29/ ንዑስ አንቀጽ /4/ ስር በተደነገገው መሠረት የከተማው የቦታ ማስለቀቅና የካሣ ጉዳዬች ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ የካሣ አከፋፈልን አስመልክቶ በሰጠው ውሣኔ ላይ የሚቀርብ ይግባኝ፤ እና

e/ with the exception of the decided cases under Article /13/, proclamation No 151/2007 issuing of these revised councils Establishment to be investigated, in case of kebele social councils, other offences of violation of regulation stipulated in the Federal criminal law of 7th and 8th books. ( from 734 -865);

B**. The following new Articles /58/ and /60/ are incorporated next to Article /57/ of this proclamation, in case of incorporation of these new provisions, provisions from Article /58/upto /71/ are arranged forward from Article/59/ upto Article /73/**

## 58)Additional Power of the Court in Appealate

The urban cases court shall have a power of jurisdiction with appeal of additional cases stipulated herein under, with is hearing of appealate:

1. pursuant to the provision of sub- article /4/ of Article /29/of the issued proclamation No.721 /2012 of the withholding urban land , appealate that shall be submitted on decisions that the urban land expropration and compensation cases appealate hearing commission rendered, with regard to disburssement of compensation; and,

2. በብሔራዊ ክልላዊ መንግስቱ የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 76/1994 ዓ.ም /እንደተሻሻለ/ አንቀጽ /113/ ንዑስ አንቀፅ /1/፣ በተርን ኦቨር ታክስ አዋጅ ቁጥር 83/1995 ዓ.ም /እንደተሻሻለ/ አንቀፅ /21/ ንዑስ አንቀፅ /4/፣ በኤክሣይዝ ታክስ አዋጅ ቁጥር 103/1996 ዓ.ም /እንደተሻሻለ/ አንቀጽ /18/ ንዑስ አንቀጽ /4/ እና ስለቴምብር ቀረጥ አከፋፈል በወጣው አዋጅ ቁጥር 31/1991 ዓ.ም አንቀጽ /9/ (በአዋጅ ቁጥር 168/2002 ዓ.ም አንቀጽ /19/ እንደተሻሻለ) ስር በተደነገገው መሠረት የከተማ አስተዳደሩ የግብር ይግባኝ ሠሚ ጉባኤም ሆነ የገቢዎች ባለስልጣን በሚሰጧቸው ውሣኔዎች ላይ የሚቀርብ ይግባኝ፡፡

2. pursuant to the provisions of National Regional State Income Tax Proclamation No. 76/2002 (as ammended) of sub –article /1/ of Article /113/, sub-article /4/ of Article /21/ of the Turnover Tax Proclamation No. 83/2003 (as ammended ), Sub-article /4/ of Article /18/ of the Exise Tax Proclamation No. 103/2004 (as ammended), and Article/9/ of the issued Proclamation No. 31/1998 to Stamp Duty, (Article /19/ of Proclamation No. 168/2010(as ammended) to be submitted appeals on decisions, rendered by the urban administration tax appealate hearing commission, as well as, the revenues authority.

## 59) የግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ውሣኔን በመቃወም ስለሚቀርብ ይግባኝ

1. የከተማ ነክ ጉዳይ ፍ/ቤቶች በተቋቋሙባቸው ስፍራዎች በክልሉ የገቢ ግብር፣የተርን ኦቨር ታክስ፣ የኤክሣይዝ ታክስም ሆነ የቴምብር ቀረጥ ማስከፈያ አዋጆች መሠረት የየከተማ አስተዳደሮቹ የግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤዎች ወይም የገቢዎች ባለስልጣን በሚሰጧቸው ውሣኔዎች ላይ ቅር በመሰኘት ቀደም ሲል ለየዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤቶች ቀርበው ይሰሙ የነበሩ የይግባኝ አቤቱታዎች ይህ አዋጅ ከፀናበት ቀን ጀምሮ ለከተማ ነክ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤቶች እየቀረቡ ይዳኛሉ፣

## 59) Submitting Appealate in Contravene with the Decision of the Tax Appealate Hearing Commission

1. Pursuant to the proclamations of the Regional Income Tax,Turn over Tax, Exise Tax, as well as, the Stamp Duty Tax, on places that the urban case courts established , the appealing cases that were submitted and heared by zone high courts previusly by requesting their complaints, on the rendered decisions by each city administration tax appealate hearing commissions, or the revenues authotity, shall be submitted to the urban appealate hearing courts and decided starting from the approval of this proclamation;

2. የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ /1/ ድንጋጌ ቢኖርም እንጥልጥል ጉዳዮች በየተያዙባቸው መደበኛ ፍ/ቤቶች መታየታቸውን ቀጥለው በዚያው በኩል የመጨረሻ እልባት እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡

## 60) <u>በተዛማጅ ህጐች ስለመስራት</u>

አግባብ ያላቸው የፍትሐብሔር እና የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ህጋጋት እንዲሁም የተሻሻለው የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 223/2007 ዓ/ም ድንጋጌዎች ለከተማ ነክ የመጀመሪያ ደረጃም ሆነ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቶች በተመሣሣይ ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል።

## 3 <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በክልሉ መንግሥት ዝክረ-ህግ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

ባህር ዳር
ሰኔ 06 ቀን 2007 ዓ/ም
ገዱ አንዳርጋቸው
የአማራ ብሔራዊ ክልል
ፕሬዝደራት



2. Notwithstanding the provision of sub article /1/ of this Article, pending cases shall be seen with the regular courts, that held previously and be finalized in that way.

## 60) <u>Working with Related Laws</u>

The appropriate of civil and criminal procedure laws, as well as, the Revised Amhara National Regional State Courts Establishment Proclamation No. 223/2014 provisions, shall have a similar applicability to the urban first instance, as well as, appealate courts.

## 3. <u>Effective Date</u>

This proclamation shall come into force as of the date of its publication in the Zikre Hig Gazzettee of the Regional State.

Done at Bahir Dar,
This 13th day of May, 2015
Gedu Andargachew
President of the Amhara National Region